# አይደል አልጋ ባልጋ

ትግል መራራ ነው ፤ ውጣ ውረድ ያለው
ቢጎረብጥ እንጂ ፤ ምንም ምቾት የለው
እራብና ጥማት ፤ ዘወትር ሳይለየው
የጥይት እረመጥ ፤ እሳት እያጋየው
ወድቆ ሲነሳ ነው ፤ ብርሃን የሚያየው
ራዕይ ሰንቀቆ ፤ በጽናት ለመጓዝ
በአላማህ ቆርጠህ ፤ ቀጥ በልና ያዝ
ትግል ፤ ሠርግ አይደለም ፤ አያሻህም ጉዝጓዝ ።

ጉልበትን ይበላል ፤ አጥንትን ያደቃል
ፈተናው ብዙነው ፤ ይበርዳል ይሞቃል
ውጣ ውረድ አለው ፤ መች ባጭር ያበቃል
ጽናትና አላማን ፤ ብርታት ይጠይቃል ።

የነጻነት ትግል ፤ መሰረት ጥንስሱ
ጸረ ህዝብን ታግለው ፤ እስኪደመስሱ
መሳደድ ፤ መታሰር ፤ መገደል ነው ምሱ
ካለሙት አላማ ፤ ከግብ እስኪደርሱ ።

ትግል አይገባም ፤ ምቾትን ፍለጋ
ነግዶ ሊተረፍ ፤ ሊኮን ባለጸጋ
አይረማመዱት ፤ አይደል ፤ አልጋ ባልጋ
ከግራና ከቀኝ ፤ ጠላት እያሰወጋ
ውድ ህይወትን ፤ ሳይቀር ፤ ይጠይቃል ዋጋ ።

ታዛቢው

February, 18, 2010